
# እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2019 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክረው ተስተዉለዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በትግራይ ክልል ምስራቃዊ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ እና ምስራቅ አማራ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በአፋር እና ሱማሌ ክልሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በኮምቦልቻ 35.9፣ በዱብቲ 50.6፣ በድሬዳዋ 34.2፣ በአሶሳ 32.3፣ በሻምቡ 50.0 እና 31.0፣ በሊሙገነት 82.4 እና 33.6፣ በጅማ 31.6፣ በኩሉምሳ 47.3፣ በሀዋሳ 70.2፣ በወራቤ 45.5፣ በተርጫ 60.0፣ በምዕራብ አባያ 38.0፣ በደሎመና 149.5፣ 40.3 እና 30.3፣ በአቦምሳ 107.1፣ በደብረሲና 92.6፣ በዲክሲስ 54.6፣ በአይሻ 35.4፣ በሞጣ 30.3 እና 33.7፣ በቴፒ 45.0፣ በቡርጂ 33.0፣ በጎዴ 30.0፣ በቡሌሆራ 49.6 እና 44.4፣ በቦሬ 34.9፣ በማጂ 37.3፣ በሀገረማርያም 36.0፣ በአየሁ 32.7፣ በጨፋ 36.2፣ በደምቢዶሎ 34.0፣ በጅጅጋ 31.0፣ በጎዴ 30.0 በማሻ 60.4፣ በነገሌ 30.4 እና በሴሩ 37.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-317 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከአፋር የዞን 1 እና 3፤ ከአማራ የምስራቅ ጎጃም፣ አገው አዊ፣ ደቡብ ወሎ እንዲሁም አይከል፤ የመካከለኛውና ምስራቅ ትግራይ ሰሜናዊው ክፍል፤ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የአሶሳ፣ የቶንጎና የከማሺ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ አብዛኛው ኦሮሚያ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከሶማሌ የደገሀቡር፣ የፊቅና የአፍዲር ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ከ2-9 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር፤ ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ወሎ፣ እንዲሁም የኦሮሚያ ልዩ ዞን3፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4 እና የዞን 1 ሰሜናዊው ክፍል፤ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ምስራቃዊው ክፍል፣ የቦረናና የሰሜንና ምስራቅ ሸዋ ዞን እንዲሁም የመተከል ምዕራባዊው ክፍል ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2 ላነሱ ቀናት ያህል አግኝተዋል፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር አብዛኛው ትግራይ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሁሉም የአፋር እና ሱማሌ ክልሎች ዞኖች፣ በጉጂ፣ በጅማ፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲ እና ባሌ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀድያ፣ በወላይታ፣ በጋሞጎፋ፣ በሲዳማ እና በጌዴኦ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በጥቂት የመተከል እና ቄለም ወለጋ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።


ካርታ 1    እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ  20/2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2019 ድረስ የነበረው
የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20 /2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሁለተኛዉ የሜይ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው በተለይም በትግራይ ክልል ምስራቃዊ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ እና ምስራቅ አማራ፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በአፋር እና ሱማሌ ክልሎች ላይ የእርጥበት ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡ ይህም ሁኔታ አብዛኛው የበልግ አብቃይና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎችን ያደረሰዉ እርጥበት ዘግይተውም ሆነ ቀደም ብለው ለተዘሩት የበልግ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራትና ለቀጣይ እድገታቸው ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም በመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች የተገኘዉ እርጥበት ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር ስራ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላትና ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ የነበረ ቢሆንም፤ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረዉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ በሆሳና እና በማሻ የነበረዉ ከፍተኛ ዝናብ በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ አማራና በደቡብ ትግራይ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት መቀነስ የነበረ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለበልግ ሰበሎች እድገት በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ጎን ነበረዉ (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የሜይ የሁለተኛዉ አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በአብዛኛዉ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ መረብ ጋሽ፣ የላይኛዉና የመካከለኛዉ ዋቢ ሸበሌና ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው አዋሽ፣ የአባይ ደቡባዊ ክፍል ኪስ ቦታዎች ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ላይ እንደነበሩ መራጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ደረቅ ሁኔታ ነበራቸዉ (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31/ 2019 የሚኖረው
# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥለው የሜይ የመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ሰፊ ቦታዎችን ያካተተና የተጠናከረ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ባሌ እንዲሁም የጉጂና የቦረና ዞኖች፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ ዋግ ህምራ፣ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምሥራቅና የመካከለኛው ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ከተጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በአንጻሩ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ፣ ሲቲ፣ ኀዴ፣ ደጋሀቡር፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5 ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

# እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው
# ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በሜይ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከምስራቅ የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየቀነሰ በአንፃሩ በደቡብ አካባቢዎች ላይ የመቀጠል አዝማሚያ ሲኖረው፤ በምእራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ግን እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡ በሚቀጥሉት የሜይ ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናትም በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ሰፊ ቦታዎችን ያካተተና የተጠናከረ እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው መደበኛና አልፎ አልፎም ከመደበኛ በላይ_ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የበልግ ሰብሎች ጠቀሜታ ሲኖረው ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች፣

ለግጦሽ እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከባድ ዝናብና ቅጽበታዊ ጎርፍ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ለይ በሚገኙ ሰብሎችና በማሳዎች ላይ ውሃ በመተኛት እንዲሁም የአፈር መሸርሸር ሊያስከትል ስለሚችል የበዛውን ውሃ ከማሳ በማስወገድ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን በመስራት ከወዲሁ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በሌላ በኩል በአንዳንድ የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦታቸውን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡

## <u>እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u><br><u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት የሜይ አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃችን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት በወሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ከሚኖረው ተፅዕኖ አንጻር አብዛኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌና ተከዜ፣ ገናሌዳዋ እንዲሁም የአባይ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከከፍተኛ እርጥበት መኖር ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ትኩረትና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በጥቂት የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛው ኦጋዴንና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ የሆነ የእርጥበት መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቃማ ሁኔታ ላይ እንደሚቆዩ ይጠበቃል። በመሆኑም የተገኘውን የውሃ መጠን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡